**የመጽሐፍ ግምገማ**

**ገምጋሚ፤ ፕሮፌሰር አዱኛው ወርቁ**

**የመጽሐፍ አርዕስት፤ ፈተና**
http://www.tewodros.com

**ደራሲ፤ ቴዎድሮስ አበበ**

**የታተመበት ዓመትና በታ፤ 2005፣ ዋሽንግተን ዲሲ**

**የገጽ ብዛት፤ 141**

ቴዎድሮስ አበበ ማነው? የ«ፈተና» ደራሲ፣ ቴዎድሮስ አበበ፣ በአስተሳሰቡ በጣም የበሰለ ግለሰብ ነው። በትምህርቱም የሚያከራና የተመሰከረለት ኢትዮጵያዊ ነው። የባችለርና የማስተርስ ዲግሪ ባለቤት ከመሆኑ በተጨማሪ ለፒ.ኤች.ዲ. ዲግሪ የሚያበቃውን ትምህርት በፐብሊክ ፖሊሲና በዲቨሎፕመንት ጥናት አጠናቆ ዲሰርቴሽኑን በማዘጋጀት ላይ ይገኛል። መደበኛ ሥራውን እየሠራ ከዚህ የትምህርት ደረጃ መድረሱ የሚያስመሰግን ብቻ ሳይሆን የሚስገርምም ነው። «ከልብ ካለቀሱ እንባ አይገድም» ይሏል እንዲህ ነው።

ይህ ግለሰብ በኢትዮጵያ ጉዳይም ራሱን የቻለ ትልቅ አስተዋጽ አበርክቷል። ለምሳሌ፣ በዋሽንግቶን ዲሲና በአከባቢዋ በሚከሄዱ የበጎ አድራጎት ሥራዎች በተደጋጋሚ ተሰትፏል። የወገን ነፍስ አድን ኮሚቴ አባልና ዋና ጸሐፊ በመሆን ከማገልገሉም በላይ ኮሚቴውን ወክሎ በ2000፣ በ2001 እና በ2003 ወደ ኢትዮጵያ በመሄድ  በድርቅና በረሃብ የተጎዱ የሀገሪቱን ልዩ ልዩ ክፍሎች ተዘዋውሮ ጎብኝቷል።

ደራሲው «ፈተና» በሚለው የግጥም ስብስብ መጽሐፉ ካካተታቸው 70 ግጥሞች አብዛኞቹ ከ2000 እስከ 2005 ባሉት ዓመታት ውስጥ የተጻፉ ናቸው። ግጥሞቹ ያየውን አይቶ፣ የሰማውን ሰምቶ፣ ለአገሩና ለወገኑ ከሚያዝን ልብና ከሚጨነቅ አእምሮ የፈለቁ ግጥሞች ናቸው። የአብዛኞቹ ግጥሞች ስያሜ ገና ግጥሙ ሳይነበብ ለአንባቢ ግልጽ የሆነ ጥቆማ ይሰጣሉ። ከዚህ የሚከተሉትን የግጥም አርዕስቶች ለምሳሌ መጥቀስ ይቻላል። «ይቻል ይሆን? ቁጭት፣ ከበደኝ፣ ጽናት ስጠኝ፣ ተለመነን፣ የዕንባ ጉዞዎች፣ መፍትሔ፣ የመሪ ያለህ! ግጭት፣ ይገርማል! እብደት፣ ጩኸት፣ ሕልም»።

ደራሲ ቴዎድሮስ አበበ በግጥሞቹ በአብዛኛው ኢትዮጵያዊ አእምሮ ውስጥ የሚጉላሉ ጥያቄዎችን ያነሳል። ክፉና በጎ ለይቶ የሚያስተምር መንፈሳዊ ባለጸግነት፣ ተፈጥሮ ሁሉን አሟልቶ የሰጣትና የምታኮራ ሀገር፣ የሚያስፎክር ታሪክና ባህል፣ ጠንካራና ታታሪ ሕዝብ እያለን ለምን ለጉስቁልናና ለሰቆቃ ተዳረግን? ካለፈው ታሪክና ልምድ ተምረን ማደግና መሻሻል ስንችልና ሲገባን ከጥፋት ላይ ጥፋት እያከልን፣ ከበደል ላይ በደል እየጨመርን፣ ከድርቅና ከረሃብ ላይ ጠብና ጦርነት እየጫርን ለምን እናልቃለን? ለምንስ እንተላለቃለን? እያለ ይጠይቅና «በዘሬው ትውልድ ላይ የማይጠፋ ጠባሳ ትቶ እያለፈ ያለው፤ ማንነትንና እምነትን የሚሸረሽረው ዘመን-አመጣሽ ክሕደት ነው» በማለት ይመልሰዋል።

«ጥያቄ» በሚል ርዕስ የተቀናበረው ግጥም ይኸን እውነታ ለማጉላት እንደዚህ ይላል፤

የትውልዴን እጣ ሰስብ የተጫነውን መከራ
የተሸከመውን ፍዳ ያልተወጣውን አደራ
«ለምን»? እላለሁ ለራሴ ሕሊናዬ ሲታገለኝ
የማንነቴ መሽርሽር በቁጭት ፍም ሲያቃጥለኝ
ለምን?
ለምን ይሆን ይሄ ትውልድ በግፍ ዕንባ መነከሩ?
ሕልውናው መሠረቱ በፈተና መታጠሩ
ለምን ይሆን የሀገሬስ አንድነቷ መፈለሱ?
ዳር ድንበሯ መደፈሩ ኬላው በሯ መገርሰሱ
ለምን ይሆን በኔው ዘመን ባንዲራዬ መቀደዱ?
ታሪክ ቅርሴ መመዝበሩ ዜግነቴ መዋረዱ
ለምን?
ለምን?

«ፈተና» ማንኛውም ኢትዮጵያዊ ሊያነበው የሚገባ ታሪካዊና ኪነ–ጥበባዊ መጽሐፍ ነው። ከፍሬ ነገሩ እስከ ግጥም አወቃቀሩ፣ ከቃላት አመራረጡ እስከ ስንኝ አጣጣሉ ይህ ቀረው የማይባል መጽሐፍ ነው። አንዳንዶቹ ግጥሞች አጠር፣ አንዳንዶቹ ደግሞ ረዘም ያሉ ናቸው። ታዲያ ሁሉንም ግጥሞች የሚያያይዛቸው ዋና መሪ ሀሳብ በኢትዮጵያና በኢትዮጵያውያን ላይ እያንዣበበ ያለው የጥፋትና የክህደት ደመና ነው።

ደራሲ ቴዎድሮስ አበበ የኢትዮጵያንና የልጆቿን እንባ፣ የመሪዎቿን ጭካኔና ደባ፣ የዜጎቿን እሥራትና ስደት፣ የንጹሐን ግለሰቦችን አፈናና ሞት፣ በሰበብ አስባቡ በተደጋጋሚ የሚፈጠረውን ጦርነትና ግጭት፣ ተፈጥሮ የሚያመጣውን ርሃብና እልቂት በተለያዩ ግጥሞቹ ከዳሰሰ በኋላ ምኞቱን፣ ተስፋውን፣ እንደዚሁም ተማጽኖውን ገጽ 141 ላይ «ሕልም» በሚለው ግጥሙ ያጠቃልለዋል።

ምን ትመኛለህ ብትሉኝ
መመኘቴ ከልከፉ
አገር–በቀል ሥርዓት
በኢትዮጵያ ልክ የተሰፋ
ለባህሏ የሚስማማ
የብስ ውሐዋን የሚያለማ
እምነቷን የሚያዳብር
ታሪክ ቅርሷን የሚያከብር
ማኅበራዊ ትስስሯን
የፈሪሀ እግዚአብሔር ውርሷን
የሚያጸና ...
ኢትዮጵያዊ ፍልስፍና
ነው ለማየት የምመኘው
የማልመው።
«ማርክሲዝም»
«ከሙኒዝም»
«ፌዴራሊዝም»

ሌላም « ኢዝም»
እንደ ሸቀጥ ያራከሰት የባዕድ ፖለቲካ ...
በኢትዮጵያ« ኢዝም» እንዲተካ
ነው ለማየት የምመኘው
የማልመው።

ደራሲው በዚህ እድሜው ስለፍቅርና ስለፍቅረኛው መጻፍና ማዜም ሲገባው ይኸን የመሰለ ከባድ የሀገርና የወገን ጭንቀት በለጋ ትከሻው ተሸክሞ እንዲተክዝ መገደዱ እጅግ በጣም ያሳዝናል። ከእሱ የእድሜ ክልል በላይ ያለው ትውልድ በፖለቲካ ጊያ እየተሸመደመደ ለራሱም ሆነ ለሚቀጥው ትውልድ የጥፋት ጎተራ መሆኑም የበለጠ ያሳዝናል። «አባት ያበጀው ለልጅ ይበጀው» እንዲሉ እያንዳንዱ ትውልድ ያለፈው ትውልድ ባለዳ፣ የሚመጣው ትውልድ ባለውለታ መሆን ይገባው ነበር። ካለፈው ትውልድ የተረከበውን አሻሽሎና አሳድጎ ለሚመጣው ትውልድ ማስረከብ ተገቢ መሆኑ እየታወቀ በአውቆ አበድነት እየተሠራ ያለው ጥፋትና ክህደት ጎልማሳውን ትውልድ «ሁለት ያጣ ጎመን» አድርጎታል። የደራሲው ትውልድም «በደረቅ አበሳ ርጥቡ ይነዳል» የሚባለው ደርሰበት ያለአበሳው ከሌላው ጋር አብሮ ያለቅሳል።

ይህ የግጥም መጽሐፍ ባንድ በኩል ወቃሽ፣ በሌላ በኩል ደግሞ መካሪ የሆነ መጽሐፍ ነው። ወቅታዊ ከመሆኑ በተጨማሪ ለኢትዮጵያ ሥነጽሑፍ ትልቅ እድገትና አስተዋጽ ስለሆነ በጽሞና መነበብ የሚገባው መጽሐፍ ነው ብዬ አምናለሁ።